ከጎቦ ዉ.ቃው ጥቅምት 2000

# <u>ቀልቀሎ ስልቻ ስልቻ ቀልቀሎ</u>

ፅንግ ድርብ ተጎናፅፈው
ከአፅናፍ-አፅናፍ ተጠራርተው
ወኔውን “ሃይሉን” ብለው
ጀግንነቱ ግማድ. . .
. . . ፍቅር ነው ፀዳሉ
ወይ ሃይሉ! ወይ ሃይሉ!
ሁሉም ተባባሉ
“ንግስቷን” አስቀምጠው. . .
 . . . በአንድ ተማማሉ
 ልጆችሽ አበሩ. . .
 “ህብረት” ይሁን አሉ
 በጥቅምት 3 እለት
 ኮሩበት፣ ታዩበት
 “ታዬን” ከሰማያት
 መረጡት፣መረቁት
 ክፍቱ ከነጀሌው…
 . . .እርማቸውን ያውጡት።

ታ ዲ ያ ማ
 የልጅሽ ድምፅ ሲሰማ
 የ”ሃይሉ” ድምፅ ሲሰማ
 ለከሃዲው ጡት ነካሽማ
 ምድር አንቀጥቅጥ ነው. . .
 . . . አለው ግርማ
 ምድረ ወያኔ ባንዳ
 መርዶውን ተራዳ
 መልእክቱ፣ ፍላፃ ቀስት
 ባንዳ፣ ዉ.ቃቢው ተነሳበት
 ድምፁም ብራቅ ሆነበት
 ወያኔንም ቆጠቆጠው

ከጎቦ ዉ.ቃው

ባንዳን ሁሉ ምን ይዋጠው?
ያንን "ክፍቴ" ብርክ ያዘው
ወትሮም እንደለመደው…
በሬ ጅብ ወለደን…
…መለከቱን ነፋው
ጅኒው ጠራው
የእብደት መድረኩ…
"ኢትዮጵያን-ሪቪው"
እማማ ኢትዮጵያ…
እሱን ከምትወልጂው
ዉሃ ሆኖ ቢቀር፤
ዳቦም ተቆረሰ
አዲስ ስም ወጣለት
ከንግዲህ መጠሪያው
"ኢትዮጵያ-እረፊው"

እንዲያም ብሎ እንዲያ ብሎ
ቃጭል ተጨምሮ በደምባራ ብቅሎ
በ"ፅጌ" አንቀልባ ታዝሎ
ይሄ መሰሪ ገበሎ
በ "መዋ" ነቀርሳ ታጅሎ
አይኔን ግንባር ያድርገው ብሎ
ተነስቶ…ፈርጦ…ዘሎ
እንደሙቀጫ ተንከባሎ
ታዲያ ምን ይሉታል?
ባንዳማ! ባንዳ ነው!
ቀልቀሎም-ስልቻ!፤ስልቻም-ቀልቀሎ!።

እ ና ማ  እማማ

ምን ትይዋለሽ ይሄን ፍጡር?
ሃፍረቱንም ያልሸፈነ . . .
በድድብናው "የጀገነ". . .
ለክፋት የሰለጠነ. . .
እሳት ሳያይው ይሚያር
ሳይወዘት የሚገነትር
ደንበር…ገተር

ገተር..ደምበር
የዱራው-ገፅ ባለቤት…
ሞቶአል የቁም ሞት. . .
በ ልጆችሽ መስማማት ግና
ተነሳበት ሽርሙጥና
ክፍቴ ሳይወጋ ደማ
ደሙም ገማ ገለማ
ግን ዓይን አለው. . .አያይማ
ግን ጆሮ አለው.. . .አይሰማማ

ታዲያማ

ህሊና ልጉአም ሆኖ
እጅን አፍን ካልመራ
ባንድነቱ ገኖበት
በአገኘበት ከተዳራ
ውጉዝ ከመ-አሪዮስ
ይወገር! ይውረድ!
. . . ከእንጦሮጦስ
መሃረነ ክርስቶስ

ከነበ ወቃው